# የገቢዎች ሚኒስቴር
# መመሪያ ቁጥር 2/1996

## ስለተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም
## የወጣ መመሪያ

1. <u>አውጪው ባለሥልጣን</u>

የገቢዎች ሚኒስትር በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 21 (2) (ሐ) እና አንቀጽ 25 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

   1. በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   ሀ/ «ባለሥልጣን» ማለት የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ነው፡፡

   ለ/ «አዋጅ» ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 ነው፡፡

   ሐ/ «ታክስ» ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡

   2 በዚህ መመሪያ የተለየ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>ሎተሪዎች</u>

1. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

   ሀ/ የሎተሪ ድርጅት ማለት በአዋጅ ቁጥር 210/1973 የተቋቋመው የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ድርጅት ወይም የሎተሪ ግብይት እንዲያከናውን በብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ድርጅት የተፈቀደለት ሰው ነው፡፡

በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል

ለ/ «የሎተሪ ግብይት» ማለት በብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ድርጅት ወይም ከብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ድርጅት ፈቃድ በተሰጠው የሚካሄድ የሎተሪ ወይም የእድል ሙከራ ሥራ እንቅስቃሴ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ነው::

2. በዚህ መመሪያ በተለየ ሁኔታ እንዲፈፀም ካልተወሰነ በስተቀር የአዋጁ ድንጋጌዎች በሙሉ በሎተሪ ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

3. የአዋጁ አንቀጽ 20 የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ሊከፍለው የሚገባው ታክስ የሚሠላባቸውን አጠቃላይ ደንቦች ይደነግጋል:: በዚህ አንቀጽ መሠረት ተከፋይ የሚሆነው በአንቀጽ 7 መሠረት ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ፣ በአዋጅ አንቀጽ 21 መሠረት የተፈቀደ ተቀናሽ ከተደረገ በኋላ የሚቀረው ታክስ ነው:: ይህ የአዋጁ ድንጋጌ የሎተሪ ግብይትን ሪፖርት ማድረግን ሳይጨምር የሎተሪ ድርጅት በሚያከናውናቸው ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

4. የሎተሪ ድርጅት ከሎተሪ ቲኬቶች ሽያጭ ከሚገኘው ገቢ ለእጣ አሸናፊዎች ተከፍሎ የሚቀረውን በሚያስገኝ የትርፍ ህዳግ ሥርዓት የሚሠራ ነው:: በሎተሪ ተሳታፊ ለመሆን ማናቸውም ሰው የሚከፍለው ገንዘብ አገልግሎት ለማግኘት እንደተከፈለ ክፍያ ይቆጠራል::

5. ለሪፖርት አቀራረብ ሲባል፣ የሎተሪ ድርጅት በሎተሪ ግብይት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ሪፖርት የሚያደርገው ሀ(ለ-ሐ) የሚለውን ቀመር በመጠቀም ሲሆን፣

በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል



106

በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል
Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

‹‹ሀ›› የታክስ ክፍልፋይ የሆነው 15/115፣

[illegible] እና [illegible]

‹‹ለ›› የሎተሪ ድርጅት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ባከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ታክስ ሲከፈልበት የሚገባው የገንዘብ መጠን ድምር፣

‹‹ሐ›› የሎተሪ ድርጅት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ለእጣ አሸናፊዎች የከፈለው ገንዘብ ድምር ነው።

6. በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ከተከናወነ የሎተሪ ግብይት ታክስ ሲከፈልበት የሚገባው የገንዘብ መጠን በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ለሎተሪ አዟሪዎች ለወኪሎች እና ለተጠቃሚዎች ከተፈፀመ ሎተሪ ሽያጭ ከተገኘ ገንዘብ ላይ ያልተሸጡ የሎተሪ ቲኬቶች በመመለሳቸው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ለሎተሪ አዟሪዎች እና ለወኪሎች መልሶ የተከፈለ ሂሳብ ሲቀነስ የሚቀረው ነው።

7. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3(5)ሐ በተመለከተው ቀመር መሠረት ለእጣ አሸናፊዎች በጥሬ ገንዘብ ከተከፈለው በስተቀር የሎተሪ ድርጅት በአዋጅ አንቀጽ 21 በተመለከተው የሂሣብ ጊዜ ውስጥ በአዋጅ አንቀጽ 21 በተፈቀደው መጠን የታክስ ቅናሽ ሲያገኝ ይችላል።

8. የሎተሪ ድርጅት በአዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የታክስ ተቀናሽን ክፍፍሎ እንዲያቀርብ የሚጠበቅ ሲሆን፣ በአዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) ለተመለከተው ቀመር አፈፃፀም ታክስ የሚከፈልበት የሎተሪ ግብይት የሚሆነው በንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተው (ለ-ሐ) ቀመር 100/115 ይሆናል።

9. የመንግሥት መ/ቤቶች የሎተሪ ድርጅትን የሚያስከፍሉት የእቃ አገልግሎት ክፍያ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ክፍያ ተጨማሪ እሴት ታክስ ካልተከፈለበት እና የመንግሥት መ/ቤቱ ታክሱን ወይም ክፍያውን የሚያረጋግጥ የታክስ ደረሰኝ ካልሰጠ በስተቀር የታክስ ቅናሽ የሚገኝበት አይሆንም።

Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

107

10. በሎተሪ እጣው አሸናፊ ወይም አሸናፊዎች የሌሉ እንደሆነ እና ለእጣ አሸናፊ የተዘጋጀው ሽልማት ወደፊት ለሚወጣ እጣ እንዲውል የተደረገ እንደሆነ፣ ለወደፊት የሚወጣው እጣ ካልወጣ ሽልማቱ ለአሸናፊዎች ካልተሰጠ በስተቀር ለወደፊት ለሚወጣ እጣ እንዲውል ከተቀመጠው ገንዘብ ጋር የተያያዘው ሂሳብ ወይም እዳ በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 5 መሠረት በሎተሪ እንቅስቃሴው ላይ የሚከፈለው ታክስ በሚሰላበት ጊዜ ከግምት ውስጥ የሚገባ አይሆንም፡፡

11. የሎተሪው ድርጅት በሎተሪ እጣ አሸናፊ የዓይነት ሽልማት የሚሰጥ ከሆነ፣ በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 5 መሠረት በሎተሪ እንቅስቃሴ ላይ ሊከፈል የሚገባው ታክስ በሚሠላበት ጊዜ በዓይነት የሚሰጠው ሽልማት ዋጋ ከግምት ውስጥ አይገባም፡፡ ሆኖም በዓይነት የሚሰጠው ሽልማት ላይ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 መሠረት በአሸናፊው ሊከፈል የሚገባውን የገቢ ግብር የሎተሪ ድርጅቱ ለግብር ባለሥልጣኑ ስለሚከፍልና ለአሸናፊው በገንዘብ እንደተሰጠ ሽልማት ስለሚቆጠር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3(5)ሐ መሠረት ለግብር የተከፈለው ገንዘብ ብቻ ከግምት ውስጥ የሚገባ ይሆናል፡፡

12. የሎተሪው ድርጅት በዓይነት የሚሰጠውን ሽልማት እንደግብአት በመውሰድ በአዋጅ አንቀጽ 21 በተደነገገው መሠረት ሽልማቱን በሚገዛበት ጊዜ የከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ እንዲሆንለት መጠየቅ ይችላል፡፡

13. በአዋጅ አንቀጽ 21 ተቀናሽ ስለማይደረጉ ወጪዎች የተደነገገው ለእጣ አሸናፊዎች በዓይነት የሚሰጡ ሽልማቶችን በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የጉዞ ወኪሎች እና የአስጎብኚዎች አገልግሎት

1. ነዋሪ የሆነ የጉዞ ወኪል ወይም አስጎብኚ ድርጅት የሚባለው በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ እና በኢትዮጵያ ውስጥ በጉዞ ወኪልነት ወይም በአስጎብኚነት የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ የተሠማራ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነና በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ በጉዞ ወኪልነት ወይም በአስጎብኚነት የሥራ እንቅስቃሴ ላይ የተሠማራ ሰው ነው፡፡



በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል
Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

2. ነዋሪ የሆነ የጉዞ ወኪል በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው ከኢትዮጵያ ውጪ የሚደረጉ ጉዞዎችን ያመቻች እንደሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚደረጉ ጉዞዎች የተደረገው ክፍያ (የዓለም ዓቀፍ የአየር ትራንስፖርት፣ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚደረግ የሆቴል እና የምግብ አገልግሎት ጨምሮ) አዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና 2(ለ) መሠረት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግበታል። የጉዞ ወኪሉ ጉዞዎቹን በማመቻቸት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ክፍያ ወይም ኮምሺን በኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወነ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ነው።

3. አስጉብኚ ድርጅቶች የአገልግሎቱ ቀጥታ አቅራቢ ሲሆኑና አገልግሎቱም ታክሱ የሚመለከተው ከሆነ ሰብስቦ ገቢ ያደርጋል ሆኖም አገልግሎቱ በሶስተኛ ወገን የሚሰጥ ከሆነ ግን አስጉብኝው ድርጅት የሚያገኘው የኮሚሽን ድርሻ ላይ የተ.እ.ታ ይከፍላል።

4. የጉዞ ወኪሉ ደንበኞችን ከቦታ ወደ ቦታ እንዲያዘዋውር የመደበው ሠራተኛ ላገኘው የሆቴልና የምግብ አገልግሎት የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት ተቀናሽ አይደረግም።

5. ነዋሪ የሆነ የጉዞ ወኪል አስጉብኚ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የጉዞ ወኪል ወይም አስጉብኚ የኢትዮጵያ ወኪል በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ሰው የአገር ውስጥ ጉብኝት ያመቻች እንደሆነ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ከሚደረግባቸው እንደዓለም አቀፍ ትራንስፖርት ካሉ አገልግሎቶች በስተቀር ከጉዞው ጋር በተያያዘ የሚሰጡ አገልግሎቶች ታክስ የሚከፈልባቸው ይሆናል።

6. በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ የጉዞ ወኪል ወይም አስጉብኚ ስም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች በአዋጁ አንቀጽ 7 ወይም 8 መሠረት ከታክሱ ነፃ የተደረጉ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግባቸው ካልሆኑ በስተቀር ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ናቸው።

የገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል
... Documentation Section

109

7. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው (እንደ ውጭ አገር አስጎብኚ ድርጅት ወይም የጉዞ ወኪል ያለ) በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግን ጉብኝት የሚጨምር (እንደ አደን ጉዞ የመሳሰሉ) ጉዞ ያመቻቸ እንደሆነ በአገር ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ታክስ ይከፈልበታል::

8. በተራ ቁጥር 7 ከተመለከተው ጉዞ ጋር በተያያዘ በውጭ አገር ያለው ሰው ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈል ኮሚሽን ወይም ለዓለም አቀፍ ትራንስፖርት የሚከፈል ክፍያ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግበታል በውጭ አገር ያለ የጉዞ ወኪል በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚሰጥ የጉዞ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚገኘው ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ እና አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚገኝ ሰው በተሰጠ አገልግሎት የተገኘ በመሆኑ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግበታል::

9. በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው ወኪል ሆኖ የሚሠራ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የጉዞ ወኪል ወይም አስጎብኚ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግን ጉብኝት ያመቻቸ እና ለዚህም አገልግሎቱ ኮሚሽን የተከፈለው እንደሆነ በኢትዮጵያ የሚገኘው የተመዘገበ ሰው ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ከሚደረግበት የሥራ እንቅስቃሴ ለምሳሌ በውጭ አገር ላለው ወኪል ከሚከፈል ኮሚሽን እና ከዓለም አቀፍ ትራንስፖርት አገልግሎት ውጪ በስተቀር በጉዞው ወጪ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል አለበት::

## 5. <u>ያገለገሉ ዕቃዎች ሽያጭ</u>

1. ያገለገሉ ዕቃዎችን በመሸጥ ተግባር ላይ የተሠማራ የተመዘገበ ሰው እነዚህን ዕቃዎች የገዛው ከተመዘገበ ወይም ካልተመዘገበ ሰው ሊሆን ይችላል:: ከተመዘገበ ሰው በተገዙ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን፣ ካልተመዘገበ ሰው በተገዛ ዕቃ ላይ የተከፈለ ታክስ ግን ተቀናሽ አይደረግም::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3-6 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ያገለገሉ እቃዎች በመሸጥ ተግባር ላይ የተሠማራ የተመዘገበ ሰው በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት የታክስ ማቀናነስ እንዲደረግለት ሊጠይቅ የሚችለው በሚከተለው ሁኔታ ነው፣

ሀ/ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት እቃዎቹ በ15% የማስከፈያ ልክ ታክስ የማይከፈልባቸው ከሆነ የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ከተመዘገበ ሰው ታክስ በሚከፈልበት ግብይት በኢትዮጵያ ውስጥ የገዛቸው ታክስ ስሚከፈልበት ግብይት የሚውሉ ያገለገሉ እቃዎች 15/115 በሆነ የታክስ ክፍልፋይ ሲሰላ ከሚደረስበት ሂሳብ ጋር እኩል ሊሆን የሚችል ከሚከተሉት አነስተኛው የገንዘብ መጠን፣

I. ለእቃው ከተከፈለው የገንዘብ መጠን፣ ወይም
II. ታክስን ጨምሮ ከእቃው የገበያ ዋጋ፣

ለ/ ግንኙነት ላለው ሰው በሚቀርቡት እቃዎች ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ያልበለጠ እስከሆነ ድረስ በአዋጅ በተደነገገው መሠረት እቃዎቹ በ15% የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው ከሆነ የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ከተመዘገበ ግንኙነቱ ያለው ሰው ታክስ በሚከፈልበት ግብይት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የገዛቸው ታክስ ስሚከፈልበት ግብይት የሚውሉ እቃዎች 15/115 በሆነ የታክስ ክፍልፋይ ሲሰላ ከሚደረስበት ሂሳብ ጋር እኩል ሊሆን የሚችል ከሚከተሉት አነስተኛ የገንዘብ መጠን፣

I. ለእቃው ከተከፈለው የገንዘብ መጠን፣ ወይም
II. ታክስን ጨምሮ ከእቃው የገበያ ዋጋ፣

ሐ/ በውሉ መሠረት ሳልፈፀመው የዱቤ ሽያጭ በቀረበው እቃ ላይ ሲከፈል ከሚገባው ታክስ ያልበለጠ እስከሆነ ድረስ በአዋጁ በተደነገገው

Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

771

መሠረት እቃው 15% የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ከሆነ የተመዘገበው ሰው በውሉ መሠረት ካልፈፀመ የዱቤ ገዥ በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ታክስ በሚከፈልበት ግብይት መልሶ ለተረከበው ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት ለሚውል ያገለገለ እቃ ከዋጋው 15/115 ከሆነ የታክስ ክፍልፋይ ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ መጠን፣

መ/ የመድን ዋስትና ለተሰጠው ሰው በሚቀርበው እቃ ላይ ከሚከፈለው ታክስ የልበለጠ እስከሆነ ድረስ የተመዘገበ የኢንሹራንስ ድርጅት ታክስ በማይከፈልበት ግብይት የመድን ዋስትና ከተሰጠው ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የተረከበው ያገለገለ እቃ፣

I. በካሣ ክፍያ ጥያቄ ምክንያት የተገኘ ከሆነ፣

II. በአዋጁ በተደነገገው መሰረት በ15% የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ከሆነ፣

III. ታክስ በሚከፈልበት ግብይት መልሶ ለመሸጥ የሚውል ከሆነ፣

የእቃው ዋጋ 15/115 ከሆነ የታክስ ክፍልፋይ ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ መጠን፣

3. ይህ መመሪያ ለኪራይ በሚውሉ ያገለገሉ እቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

4. ያገለገሉ እቃዎች ሽያጭ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግበት ከሆነ ታክስ በሚከፈለበት ግብይት የዚህ ዓይነቶቹን ያገለገሉ እቃዎች ሽያጭ የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የታክስ ማቀናነስ እንዲደረግለት ሊጠይቅ አይችልም።

Ministery of Revenues
... and Documentation Section

(112)

5. ያገለገሉ እቃዎች የሚባሉት የእቃዎቹ ባለቤት በነበረ ሰው አዲስ እቃ ሆነው እንዲቆጠሩ በማያስችል ሁኔታ ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ለተለየ አገልግሎት በሚውል መልክ የተዘጋጁ ወይም በመጋዘን ተቀምጠው የቆዩትን ጨምሮ በሌላ ባለቤት ሥር የነበሩ፣ የተሰበሱ ወይም ጥቅም ላይ የዋሉ እቃዎች ናቸው።

6. የሚከተሉት ያገለገሉ እቃዎች አይባሉም፦

ሀ/ ከከበረ ብረት የተሠሩ ያገለገሉ እቃዎች ወይም

ለ/ ከወርቅ፣ከብር፣ከኘላቲኒየም ወይም በሚያስፈልገው ጥራት የተሠራ ከሆነ የከበረ ብረት ከሚሆን ከማናቸውም ሌላ እቃ የተመረተ ወይም የተሠራ ያገለገለ እቃ፣

ሐ/ የቁም ከብት፣

7. በዚህ መመሪያ መሠረት የታክስ ማቀናነስ ሲፈቀድ የሚችለው፣ የታክስ ቅናሽ እንዲደረግለት የሚጠይቀው የተመዘገበ ሰው፣ አቅራቢው ለተመዘገበው ሰው የሸጣቸውን እቃዎች የገዛው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ መሆኑን እና ታክሱ መከፈሉን የሚያረጋግጡ የፁሑፍ መረጃዎችን እንዲሁም በታክሱ ባለሥልጣን ወይም በዚህ መመሪያ እንዲቀርቡ የሚጠየቁ መረጃዎችን ካቀረበ ብቻ ነው።

8. የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቀርበውን የታክስ ማቀናነስ ጥያቄ የሚደግፉ መረጃዎች ላይ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ የታክስ ማቀናነስ ጥያቄ ያቀረበው የተመዘገበ ሰው የታክስ ተቀናሽ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት ይኖርበታል።

9. የተመዘገበው ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት የታክስ ማቀናነስ እንዲፈቀድ የሚቀርበውን ጥያቄ የሚደግፉ ያገለገሉ እቃዎች ያቀረበለትን ሰው ስም እና

Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

113

አድራሻ፣ የአቅራቢውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር / የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌለው ከሆነ የመታወቂያ ቁጥሩን/፣ እቃዎቹ የተገዙበትን ቀን፣የእቃዎቹን ዝርዝር መግለጫ፣የእቃዎቹን ብዛት ወይም መጠን ጨምሮ የግብይቱን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳዩ መረጃዎችን መያዝ ያለበት ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ፣

ሀ/ በአንቀጽ 5(2)(ሀ) ስተገለፀው ግብይት ለእቃው የተከፈለው ዋጋ እና ትክክለኛነት የገበያ ዋጋ፣

ለ/ በአንቀጽ 5(2)(ለ) ለተገለፀው ግብይት የተከፈለውን ታክስ ልክ፣የእቃዎቹን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፣ እና ግንኙነት ባለው ሰው የተከፈለውን ታክስ ልክ፣

ሐ/ በአንቀጽ 5(2)(ሐ) ለተገለፀው ግብይት መልሶ የተረከባቸውን እቃዎች ዋጋ እና በውል በገባው ግዴታ መሠረት ያልፈፀመውን የዱቤ ገዥ እቃዎቹን ሲገዛ የከፈለውን ታክስ፣

መ/ በአንቀጽ 5(2)(መ) ለተገለፀው ግብይት በመድን ካሣው ጥያቄ ምክንያት የተረከባቸውን እቃዎች ዋጋ እና የመድን ዋስትናው ተጠቃሚ እቃዎቹን ሲገዛ የከፈለውን ታክስ፣

10. የተከፈለው የገንዘብ መጠን ወይም የገዛቸው እቃዎች ዋጋ ከብር 50 የማይበልጥ ከሆነ የተመዘገበው ሰው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች እንዲይዝ አይገደድም።

11. በንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት የሚቀርቡ መረጃዎች የአቅራቢው ፊርማ የሠፈረባቸው መሆን አለባቸው።

6. የኮሚሽን ወኪሎች እና ደላሎች

1. የኮሚሽን ወኪሎች እና ደላሎች ለሚሰጡት አገልግሎት የሚከፈላቸው ኮሚሽን፣ የማበረታቻ ክፍያ፣ ቦነስ ወይም ሌላ ማናቸውም ክፍያ ታክስ በሚከፈልበት ግብይት የተገኘ ክፍያ ተደርጐ ይወሰዳል። የኮሚሽን ወኪሉ ወይም ደላላው ራሱን ችሎ የሚሠራ ወይም በተለመደው የወካይ እና የተወካይ ግንኙነት በወካዩ ሥር ሆኖ የሚሠራ ቢሆንም የአዋጁ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

2. የኮሚሽን ወኪል ወይም ደላላ አገልግሎቱን የሰጠበት ጊዜ ነው ተብሎ የሚወሰደው በአዋጁ አንቀጽ 11 የተደነገገው ጊዜ ነው። በአዋጁ አንቀጽ 11 በተደነገገው መሠረት ክፍያ በተፈፀመ ወይም አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ የኮሚሽን አገልግሎት መስጠቱን በተፋጠነ ሁኔታ የማስታወቅ ግዴታ ካልኖረ በስተቀር የኮሚሽን ወኪሎች ወይም ደላሎች የሚያከናውኑት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ሪፖርት የሚደረገው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ይሆናል።

3. የተመዘገበ የኮሚሽን ወኪል ወይም ደላላ፣ ኮሚሽን፣ የማበረታቻ ክፍያ፣ ቦነስ ወይም ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዘ ሌላ ማናቸውም ክፍያ የተቀበለ እንደሆነ፣ የኮሚሽን ወኪሉ ወይም ደላላው ለአገልግሎቱ ለተቀበለው ክፍያ የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

4. የተመዘገበ የኮሚሽን ወኪል ወይም ደላላ በአዋጁ አንቀጽ 21 በተፈቀደው መሠረት ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት እንዲውሉ በፈፀማቸው ግዥዎች ላይ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ተቀናሽ ይደረግለታል።

5. የኮሚሽን ወኪሉ ወይም ደላላው በተቀበለው ኮሚሽን ወይም ሌላ ማናቸውም ክፍያ ላይ ማስተካከያ (ለውጥ) የተደረገ እንደሆነ የኮሚሽን ወኪሉ ወይም

የገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል
Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

115

ደሳሳው በአዋጁ አንቀጽ 13 በተደነገገው መሠረት የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ሰነድ መስጠት ይችላል።

7. <u>የታክስ ማቀናነስ አፈፃፀም</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 21(2) ተቀናሽ እንዲህን የሚፈቅደው የተመዘገበ ሰው ታክስ ስሚከፈልበት ግብይት እንዲውሉ ወደአገር ባስገባቸው እና ከአገር ውስጥ በገዛቸው ላይ የከፈለውን ታክስ ብቻ ነው። ታክስ ስሚከፈልበት ግብይት እንዲውሉ ወደአገር በገቡ ወይም ከአገር ውስጥ በተገዙ ላይ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ የሚደገር ሲሆን፣ ከታክሱ ነፃ ስሆኑ ግብይቶች በዋሉ ወደአገር በገቡ ወይም ከአገር ውስጥ በተገዙ ሳይ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም። በከፊል ታክስ ስሚከፈልበት ግብይት በከፊል ደግሞ ከታክሱ ነፃ ስሆነ ግብይት በዋሉ ሳይ የተከፈለውን ታክስ የተመዘገበ ሰው በዚህ መመሪያ በተመለከተው የማከፋፈል ዘዴ መሠረት አስልቶ ማቅረብ አለበት።

2. ለአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) አፈፃፀም በከፊል ታክስ ስሚከፈልበት ግብይት በከፊል ደግሞ ከታክሱ ነፃ ስሆኑ ግብይቶች በዋሉ ወደአገር በገቡና በአገር ውስጥ በተገዙ ሳይ የተከፈለውን ታክስ የተመዘገበው ሰው ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሠረት አስልቶ ማቅረብ አለበት።

$$ተ = ሀ \times ለ/ሐ$$

ስዚህ ስሌት አፈፃፀም፣

‹‹ተ›› ተቀናሽ (ክሬዲት) ሲደረግ የሚገባ ታክስ ልክ

‹‹ሀ›› በከፊል ታክስ በሚከፈለበት በከፊል ደግሞ ከታክሱ ነፃ በሆኑ ግዥዎች ሳይ የተከፈለ ጠቅላላ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣

«ለ» የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ነው::

«ሐ» የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ያከናወናቸው ጠቅላላ አቅርቦቶች ዋጋ ነው::

3. በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 7(2) በተመለከተው ለ/ሐ ቀመር መሠረት ሲሰላ የሚገኘው ውጤት 0.90 በላይ ከሆነ የተመዘገበው ሰው በአዋጁ አንቀጽ 2(ሐ) በተመለከተው መሠረት በአገር ውስጥ በገዛቸው ወይም ከውጭ አገር ባስገባቸው ዕቃዎች ላይ የከፈለው ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ይደረጋል::

4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7(2) የተመለከተው ቢኖርም የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልባቸው እና ከታክሱ ነፃ የሆኑ ግብይቶች የሚያካሂድ ከሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ተቀናሽ የሚደረገው ታክስ ተገቢ መስሎ በታየው ሌላ ስሌት እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል::

8. <u>የሃይማኖት ድርጅቶች ተነጣጥለው የሚመዘገቡበት ሁኔታ</u>

1. የሃይማኖት ድርጅት ከአምልኮት ጋር በተያያዘ ከሚሰጠው አገልግሎት ውጪ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶችን የሚያካሂድ ከሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት መሆኑ የሚወሰነው ታክስ የሚከፈልበት ጠቅላላ እንቅስቃሴው ተደምሮ ነው::

2. የሃይማኖት ድርጅቱ በሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ በአንድነት አስልቶ በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ አንድ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ የሚያስቸግረው መሆኑን የታክሱ ባለሥልጣን የተረዳ እንደሆነ የሃይማኖት ድርጅቱ የተለያዩ ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ ሊያደርግ ይችላል::

የገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል
... and Documentation Section



117

3. ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት የሃይማኖት ድርጅት በሥሩ ያሉት የልማት ተቋማት ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ቅርንጫፎች ተነጣጥለው እንዲመዘገቡ ለባለሥልጣኑ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል:: ባለሥልጣኑ በዚህ ዓይነት በተናጠል ምዝገባ የሚቀርበውን ጥያቄ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ሙሉ ሥልጣን አለው::

4. የሃይማኖት ድርጅት ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ ያቀረበውን ጥያቄ ባለሥልጣኑ የተቀበለው ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ አነሳሽነት የሃይማኖት ድርጅቱ የልማት ድርጅቶች ወይም ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ ያደረገ እንደሆነ፣ የተናጠል ምዝገባ የሚከናወነው ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን ሁኔታ እና ገደብ መሠረት በማድረግ ይሆናል::

9. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከጥር 1 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥር 1 ቀን 1996 ዓ.ም.

ጌታቸው በላይ
የገቢዎች ሚኒስትር

በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን



በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Records and Documentation Section

118